በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት - *__ክፍል ፪__*


መምህር፦  ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**__E-mail:__** kesisolomon4@gmail.com


*__ቦታ፦__*  ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ጥር ፳ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# <u>በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት</u>

***<u>የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነው ትዕግሥት በሰው ሕይወት ውስጥ ያለው ደረጃ</u>***

- በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የሚገኘው ትዕግሥት ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው በምድር ባሳየን ትዕግሥት ተገልጾ ያየነው ነው፡፡

- በዚህም ሕይወት የምንታገሳቸው የምንፈራቸውን ወይም የምናከብራቸውን ብቻ ሳይሆን የሰው ወገን ሁሉ ባለመለየት የምንታገሥበት ነው፡፡

- እንዲህ ላለው የትዕግሥት ሕይወት መጥፎ የሆነ ዝንባሌ ሳይታይ በርጋታ በመራመድ ሌሎች እንዲበድሉ ምክንያት ሳይሆኑ መገኘት መለያው ነው፡፡

- በዚህም ረጅም ጊዜያትን በመውሰድና ሂደቶችንም በርጋታ በመከታተል እጅግ የላቀ ውጤት ማግኘት እንችላለን፡፡

-ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ሲያስተምራቸውም ሆነ በፊታቸው ተአምራትን ሲያደርግ በታላቅ ትዕግሥት ነበር፡፡

- መንግሥቱ ምድራዊት እንደሆነች አድርገው ሲያስቡ፣ በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታላቅ መነው ብለውም ሲጠይቁ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በበዓለ ጰራቅሊጦስ እስኪቀበሉና በመንፈሳዊው ኃይል እስኪጎለምሱ ድረስ ታግሶአቸዋል፡፡

- የተቀበሉትም መንፈስ ቅዱስ መከራን ሳይቀር የሚታገሱበት ፍሬ እንዲያፈሩ ብርታት ሰጥቷቸዋል፡፡ "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም።" ***<u>ገላ 5፡22-23፡፡</u>***

- ቅዱስ ጳውሎስ የዚህን ትዕግሥት ኃያልነት ሲያስረዳን "በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፤ ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ፤ በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ፤ ለጌታ ተገዙ፤ በተስፋ ደስ ይበላችሁ፤ በመከራ ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ፤ ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ፤ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ።" ብሎ ጽፎልናል፡፡ ***<u>ሮሜ 12፡10-13፡፡</u>***

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት

***የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነው ትዕግሥት በሰው ሕይወት ውስጥ ያለው ደረጃ***

- ከዚህ የምንረዳው ትዕግሥት ሰው በውስጡ ለእግዚአብሔርና ለሰው ወገኖችም ሁሉ ካለው ፍቅር የሚመነጭ መሆኑን ነው፡፡

- ትዕግሥት ከውስጣዊ ደስታም የሚመነጭ እንጂ በውስጥ መታወክ እያለ በውጭ በማስመሰል የምናሳየው ዓይነት “ትዕግሥት” አይደለም፡፡

- ቅዱስ ጳውሎስ በውስጡ የነበረውን እንዲህ ያለ ትዕግሥት አስመልክቶ “ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን፤ በብዙ መጽናት፥ በመከራ፥ በችግር፥ በጭንቀት፥ በመገረፍ፥ በወኅኒ፥ በሁከት፥ በድካም፥ እንቅልፍ በማጣት፥ በመጦም፥ በንጽህና፥ በእውቀት፥ በትዕግሥት፥ በቸርነት፥ በመንፈስ ቅዱስ፥ ግብዝነት በሌለው ፍቅር፥ በእውነት ቃል…” ***ካል ቆሮ 6፡4-6፡፡***
- በዚህ በሚሆነውም ችግር ሁሉ ልቡ በፍጹም ደስታ የተሞላ ነበር፡፡ “ኀዘንተኞች ስንሆን ዘወትር ደስ ይለናል፤ ድሆች ስንሆን ብዙዎችን ባለ ጠጎች እናደርጋለን፤ አንዳች የሌለን ስንሆን ሁሉ የእኛ ነው።” ***ካል ቆሮ 6፡10፡፡***

- ቅዱስ ጴጥሮስም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደውና ተቀባይነት ያለው ዋጋም የሚያስገኘውን የክርስቲያኖችን ትዕግሥት አስመልክቶ “ሎሌዎች ሆይ፥ ለበጎዎችና ለገሮች ጌቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለጠማሞች ደግሞ በፍርሃት ሁሉ ተገዙ። በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገሥ ምስጋና ይገባዋልና። ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጎሰሙ ብትታገሡ፥ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ብትታገሡ፥ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል። የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና። እርሱም ኃጢአት አላደረገም፥ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፥ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፡፡” ***ቀዳ ጴጥ 2፡18-23፡፡***
- ከዚህ የምንረዳው ቅዱሳኑ ሁሉ ከጌታችን የተማሩት ዓይነት የትዕግሥት ፍሬ የነበራቸውና ከነዚህም ቅዱሳን አንዱን የትዕግሥት ፍሬ አለህን? ብለን ብንጠይቅ የሌለውና በዚህ ለመገኘትም ረጅም መንገድ መሄድ የሚገባው መሆኑን ይነግረናል፡፡

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት

***እውነተኛ ታሪክ***

- የተወሰኑ መነኮሳት ወደ ታላቁ መቃርስ በመሄድ ከገዳማውያኑ መካከል አንዱ ወደ ባዕቱ እየመጣች የምትጉበኘው ሴት እንዳለችና ከርሷም ጋር በኃጢአት መውደቁን ገልጸው በመክሰስ ነገሩት፡፡ ቅዱስ መቃርስም ጊዜ በመውሰድ ወደ ባዕታቸው በመመለስ መነኩሴውን በጸሎት እንድያስቡ ነገራቸው፡፡

- ገዳማውያኑም ዳግመኛ በመመለስ ሴቲቱ በመነኩሴው ባዕት በዚህ ምሽት ሰዓት እንደምትገኝና ከነርሱም ጋር ወደ መነኩሴው ባዕት በመሄድ ይህንኑ እንዲመለከት ነገሩት፡፡

- ታላቁ መቃርስም ከገዳማውያኑ ጋር ወደ መነኩሴው ባዕት በመሄድ በሩን በማንኳኳት በስሙ ጠራው፡፡

- መነኩሴውም የሆነውን ነገር ስለተረዳ ሴቲቱን በጠረጴዛ (በቅርጫት) ውስጥ ደበቃት፡፡

- ቅዱስ መቃርስም ሰላምታ ሰጥቶት በጸጥታ ወደ ባዕቱ በመግባት በቅርጫቱ ላይ በመቀመጥ መነኩሴውን ‘‘ወዳጄ ሆይ፡- ሌሎች ሳይፈርዱብህ አስቀድመህ በራስህ ፍረድ፡፡’’ አለው፡፡

- ቅዱስ መቃርስ ከመነኩሴው ባዕት ሲወጣም ‘‘የሰዎችን ኃጢአት በመሰወር ጌታህን አምላክህን ኢየሱስ ክርስቶስን መስለኸዋልና ሰላምታ ይገባሃል፡፡’’ የሚል ድምጽ ሰማ፡፡

- በዚህ እውነተኛ ታሪክ ቅዱስ መቃርስ መነኩሴውን ሳያስቆጣው ሳያበሳጨውም ፈጽሞ በጽንአት በመታገስ አሸንፎት በንስሐ ወደ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመለስ የረዳው መሆኑን እንመለከታለን፡፡

- በዚህ ታሪክ አማካይነት ልናስረዳ የፈለግነው ሰው ምንም ያህል በትዕግሥት ሕይወት ቢገኝ ወደ ፍጹምነት ፈጽሞ የማይደርስ እንደሆነ ነገር ግን የትዕግሥትን ሕይወት አስፈላጊነት በጥልቀት እየተረዳ በሄደ ቁጥር ብዙ የሚቀረው መሆኑን እየተረዳ እንደሚሄድ ነው፡፡

# <u>በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት</u>

- በትዕግሥት፣ መከራን ሁሉ በመታገሥ ሁሉንም በመቻል በተገቢው ጊዜ ችግራችንን መፍታት የሚያስችለን ተግባራዊ ዕድል እንደሚኖረን መረዳት ተገቢ ነው፡፡
- ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቡድን ለተለያዩት የኤአሁድ ወገኖች (ፈሪሳውያን፣ ሰዱቃውያን…) አብዝቶ እያስተማረ ተአምራትንም በፊታቸው እያደረገ ቢመላለስም እነርሱ ግን ሰደቡት ይገድሉትም ዘንድ አሰቡ፡፡
- ጊዜው ሲደርስ ግን ንጉሡ ሥራቸው ተገቢ እንዳልሆነ ለሁሉም ግልጽ አደረገ እንዲህም አላቸው፡፡ "እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ፥ ወዮላችሁ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ። እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ፥ ወዮላችሁ፤ ስለዚህ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ። እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕርና በደረቅ ስለምትዞሩ፥ በሆነም ጊዜ ከእናንተ ይልቅ ሁለት እጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት፥ ወዮላችሁ። … እናንተ ዕውሮች መሪዎች፥ ትንኝን የምታጠሩ ግመልንም የምትውጡ። እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በውስጡ ቅሚያና ስስት ሞልቶ ሳለ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ስለምታጠሩ፥ ወዮላችሁ። አንተ ዕውር ፈሪሳዊ፥ ውጭው ደግሞ ጥሩ እንዲሆን አስቀድመህ የጽዋውንና የወጭቱን ውስጡን አጥራ። እናንተ እባቦች፥ የእፉኝት ልጆች፥ ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ? ስለዚህ፥ እነሆ፥ ነቢያትንና ጥበበኞችን ጻፎችንም ወደ እናንተ እልካለሁ፤ ከእነርሱም ትገድላላችሁ ትሰቅሉማላችሁ፥ ከእነርሱም በምኵራባችሁ ትገርፋላችሁ ከከተማም ወደ ከተማ ታሳድዳላችሁ፤ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርስባችሁ ዘንድ። እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ በዚህ ትውልድ ላይ ይደርሳል። ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ! አልወደዳችሁምም። እነሆ፥ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል።" ***<u>ማቴ 23፥13-39፡፡</u>***

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት

- ከትዕግሥትና ከጸሎት በኋላ ክርስቲያኖች ሁሉን ለመላእክቱ (ለአለቆች) በመግለጽ ገንቢ የሆነ ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ "ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።" ***ያዕ 1፡4፡፡*** በማለት እንደተናገረው መፈጸም ይኖርበታል፡፡

- ቅዱስ ያዕቆብ ትዕግሥትና ጽንአት ዋጋና ፍሬ እንዳላቸው እንዲህ በማለት ገልጾልናል፡፡ "እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ። እነሆ፥ ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሠ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል። እናንተ ደግሞ ታገሡ፥ ልባችሁንም አጽኑ፤ የጌታ መምጣት ቀርቦአልና። ወንድሞች ሆይ፥ እንዳይፈረድባችሁ እርስ በርሳችሁ አታጉረምርሙ፤ እነሆ፥ ፈራጅ በደጅ ፊት ቆሞአል። ወንድሞች ሆይ፥ የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያትን ተመልከቱ። እነሆ፥ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፥ ጌታም እንደ ፈጸመለት አይታችኋል፤ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና።" ***ያዕ 5፡7-11፡፡***

- ጻድቁ ኢዮብ የእግዚአብሔርን ስም በክፉ ሳያነሳ ያሳየው ታላቅ ትዕግሥት ዛሬ ለምንኖረው ክርስቲያኖች ታላቅ ምሳሌ ነው፡፡ የትዕግትና የጽንአት ውጤቱ ዘወትር መልካም ነው፡፡ "ኢዮብም ስለ ወዳጆቹ በጸለየ ጊዜ እግዚአብሔርም ምርኮውን መለሰለት እግዚአብሔርም ቀድሞ በነበረው ፋንታ ሁለት እጥፍ አድርጎ ለኢዮብ ሰጠው።" ***ኢዮብ 42፡10፡፡***

- በየዘመናቱ የነበሩ ቅዱሳን በትዕግሥትና በጽንአት ላሳዩት ሕይወት ዋጋቸውን ተቀብለዋል ወይም አግኝተዋል፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ በወፎጮ ፈጭተውት ሥጋውን እንደ አመድ ሲበትኑት፣ ወደ ሰባው ነገሥታት ፊት ወስደው ቢያስጨንቁት፣ በቁም ቢቀብሩት፣ መሬትን ረግጦ ሙታንን እያስነሳ በአምላኩ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለውን እምነት በማጽናት ላሳየው ትዕግሥትና ጽናት ዋጋውን ተቀብሏል፡፡ በእውነትም አእምሮውን ሳሰሰለውጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለው እምነት ባሳየው ፍቅር ሊቀ ሰማዕታት መባል የሚገባው ነው፡፡ በሀገራችንም በፋሽስት ኢጣሊያ፣ በግራኝ መሐመድ፣ በቅርቡ በአክራሪ ሙስሊሞች በጭካኔ የተፈጸመባቸውን ታግሰው ጸንተው ያለፉ ሰማዕታትም ዋጋቸውን ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቀበላሉ፡፡

- እንደዚሁ ሁሉ ሁሉም ሰማዕታት፣ ገዳማውያን፣ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችዋ መስቀሉን በመሸከም መከራን፣ ስቃይን፣ … ሁሉ በጥልቅ እምነትና ፍቅር በመታገስ ላይ ይገኛሉ፡፡

# በፈጣኑ ዓለም ውስጥ የሚፈለግ ትዕግስት

***ሰው ይህን ክርስቲያናዊ ትዕግሥት እንዴት ሊላበሰው ይችላል?***

- ክርስቲያኖች ሊላበሱት እንደሚችሉት ክርስቲያናዊ ሕይወት ትዕግሥትም እግዚአብሔር የሚሰጠው ስጦታ ወይም በረከት ነው፡፡ "በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ።" ***ያዕ 1፥17፡፡***

- በክርስቲያኖች (ኦርቶዶክሳውያን) ውስጥ በሚኖር መንፈስ ቅዱስ አማካይነት ዘወትር ስጦታው ይሰጣቸው ዘንድ ዘወትር ደጋግመው ለሚጠይቁ ወይም ስጦታውንም ለሚያደንቁ ሁሉ ይሰጣል፡፡ ይህ ስጦታ ለሚሹት ነገር በእውተን ለማያደንቁትና ለማይጠቀሙበት አይሰጥም፡፡ ስለዚህ ይህን ስጦታ ይቀበሉ/ይላበሱ ዘንድ ሰዎች ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል?

1. በመጀመሪያ ይህ ሕይወት አስፈላጊ እንደሆነ ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች ድኅነትም ጠቃሚ እንደሆነ ማመን፡፡ ጥልቅ የሆነ ትዕግሥት እንደሚያሻ ከተረዳን ሕይወትን ተስፋ ባለመቁረጥ ለመጋፈጥና ሌሎችንም እንዲበድሉ ምክንያት ሳንሆናቸው የምንራበድበት ጽኑ ትዕግሥት እንዲሰጠን ሰጪውን እግዚአብሔርን ያለማቋረጥ ዘወትር በጸሎት መጠየቅ፡፡
2. ሰዎች በውስጣቸው ያለ መንፈስቅዱስን ድምጽ ከመስማታቸው በፊት ማንኛውንም ውሳኔ ከመወሰን፣ ከመናገር መቆጠብን በቂ ጊዜ መውሰድ፡፡ በመቀጠልም ነገሮች ተካተው ጊዜው የደረሰ መሆኑን ስንረዳ እርምጃውም ጊዜውን የጠበቀ መሆኑን ስናውቅ እርምጃ መውሰድ፡፡ ስለዚህ ሰው ሰው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት መራመድ አለበት፡፡ መንፈስ ቅዱስ ጸጥተኛ፣ ርኅሩኅ ስለሆነ ማንንም ሳይወቅስ ሳይጎዳ ነገሮችንም እጅግ አስቸጋሪ ሳያደርጋቸው ነገሮችን ሊያስተካክላቸው ይችላል፡፡
3. ሰው ሐሳቡ የተረጋጋ ከሆነ ሊያስጨንቁት የሚችሉ ችግሮቹን ከፊታ ሰው ጸጥተኛና የተረጋጋ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ችግሮች ግን ተደጋግመው ሲታሰቡ ወይም ሲነጋገሩባቸው የሰውን ነርቭ የሚቆጠቁጡ ትዕግሥትንም የሚያሳጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ጸሉትና የንስሐ አባቶቻችን ታልቅ ሚና ስላላቸው ከመጸለይ ጋር ጉዳዩን ለንስሐ አባታችን ግልጽ እናድርግ፡፡
4. ለበዛው በረከቱና በረድኤቱ ለተደረገልን ጥበቃ እግዚአብሔርን ዘወትር ማመስገን፤ ይህም እግዚአብሔር በረከቱን እንዲያበዛልን ስጦታውንም እንዲጨምርልን ያደርጋል፡፡ ሶርያዊው ቅዱስ ያዕቆብ «ሳናመሰግን ቀርተን ካልሆነ በቀር የማይጨመር የማይበዛ በረከት የለም፡፡» እንዳለ፡፡

***ምን ተማርን?***

1. የትዕግሥት ሕይወት ይኖረን ዘንድ ሽተን ዘወትር መጸለይ እንደሚገባ፡፡
2. ትዕግሥት ክርስቲተተኖችን በርካታ መከራዎችን እንዲታገሡ የሚያስችል ውስታዊ ኃይል ከውስጣዊ ሰላም ካር እንደሚመመድል፡፡
3. ከመናገራችን፣ እርምጃ ከመውሰዳችን ወሳን በሆኑ ጉዳዮች ወደፊት ከመራመዳችን በፊት ዝግ ማለትን መማር እንዳለብን፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org